# የሁለት ፓርቲዎች ወግ

ዮናስ 09-04-14

የወጉ ባለቤት የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ (አንድነት) የተባሉት ፓርቲዎች ናቸው፡፡ መኢአድን ቀድሞ የአማራን ብሄረሰብ ውክልና በይፋ ይዞ ከሚንቀሳቀሰው መአህድ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የምናውቀውና በስም ህብረ ብሄራዊ ሆኖ ከተደራጀበትና በአዲስ ስያሜ ከመጣ ወቅት ጀምሮም ከሌሎቹ የተሻለ በሚባል የአባላት ብዛቱ የምናውቀው ነው፤ አንድነትም ቢሆን የ97ቱ ቅንጅት ፍንካች መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም፤ መኢአድም የቅንጅቱ አካልና አውራ የነበረ መሆኑም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፤ እናም ቅንጅቱ እንዳይሆን ሆኖ ሲፈረካከስና ሲፈነካከት መኢአድ ወደነበረበት፤ አንድነትም ከብዙ ፍንካቾች አንዱ ሆኖ ብቅ አለ፡፡ አሁን ደግሞ 10 ዓመት ጠብቀው እንደገና ሊዋሃዱ ጉሮ ወሸባዬ ወረዱና 10 ቀን ሳይቆዩ መልሰው ፈረሱ፡፡ ስለመፍረሳቸው ደግሞ አስቀድሞ ልክ እንደ 97ቱ ያዘጋጁቸውን ወጎች በዚህ አጭር ጽሁፍ  እናያለን፡፡ ወጎቻቸውንም ‹‹ወጉ ቀርቶባችሁ . . .›› እንዲሉ በገዛ ወጋቸው እናጠይቃለን፡፡

የፓርቲዎቹን ወግ የምናጠይቀው ከግለሰቦች ስብእና እና ከፓርቲዎች ውገና በፀዳ ይልቁንም ከኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አኳያ ነው፡፡ ስለሆነም በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ውስጥ መኢአድና አንድነት ያላቸውን አሰላለፍና ከሂደቱ አኳያ በዋናነት ስለገዢው ፓርቲ እና ስለሌሎቹም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያላቸውን ወግ እያወጋን እናጠይቃለን፡፡

እነዚህ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚታወቁቱ ኢትዮጵዊነትን በአፍ በማቀንቀንና በተግባር ግን ስለአንድ ባንዲራና አንድ ቋንቋ እንዲሁም አንድ ሃይማኖት ባላቸው ተጨባጭ አቋም ነው፤ ለኢትዮጵያዊነት ያላቸውን አፋዊ አቋም መሬት ለማስነካት መተባበር፣ መሰባሰብ እንዲሁም ስለእኩልነት ሌት ተቀን በመዘመር ይታወቃሉ፤ በተግባር ግን የተባበሩትን እና የተሰባሰቡ ሃይሎችን በመበተን ግንባር ቀደም ተዋናይ እንደሆኑም የምርጫ 97ቱን በሃይሉ ሻውል የሚመራ መኢአድ እና የ2007ቱን የመድረኩ አንድነት በማስታወስ ያጤኗል፡፡

እንቺው ታመጪው እንቺው ታሮጪው እንዲሉ ያኔም ሆነ አሁን ለመሰባሰብ አንደኛ ይሆኑና ለማ(መ)ፍረስም ሲጣደፉ አይጣል ነው፡፡ ግን ስለመፍረሳቸውና በምርጫ ስለመሸነፋቸው ወጉ አይቀርባቸውምና በርካታ ወነችን በማይመለከታቸው ላይ ያወጋሉ፡፡ ምርጫ ቦርድ፣ የፍትህ ተቋማት፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች፣ የፖለቲካ ምህዳር፣ ተለጣፊ ፓርቲዎች፣ ለሆዳቸው ያደሩና ፍርፋሪ ለቃቃሚ የሆኑ ፓርቲዎች ወዘተ...። ሲፋጅ በማንኪያ ሲበርድ በእጅ እንዲሉም የአንድ ወቅት ወዳጃቸው (የአውሮፓ ህብረትን እና ኤምባሲዎችን ልብ ይሏል) ነቅቶባቸው ችላ ባላቸውም ጊዜ የሽንፈታቸውም ሆነ የመበተናቸው ወግ ሆነው ይቀርባሉ፡፡

ከሰሞኑ መኢአድና አንድነት ቡሻቸውን ገጥመው የውህደትን ወግ ገና ከማውጋታቸው የወጉን አካሄድ አይተው ልክ አይደለም ያሉ ያገባኛል ባይ ዜጎችን በገዢው ፓርቲ ካድሬነትና ተለጣፊ ፓርቲነት ፈርጀው ሲያበቁ እንዲህ ሲሉ ወጋቸውን ጀመሩ፡፡ በቅርቡ ሊካሄድ ታስቦ የነበረውና በኋላ እነርሱ ‹‹በምርጫ ቦርድ›› ምክንያት ‹‹ለጊዜው›› የተቋረጠ ነው ያሉት የአንድነትና የመኢአድ ውሁድ ፓርቲ ፕሬዝዳንታዊ የምርጫ ውዝግብ፣ ‹‹እጅግ ማራኪና አስተማሪ የሆነ የዴሞክራሲያዊ ውድድር፣ የሰለጠነ የእጩዎች ደጋፊዎች ቅስቀሳ የህዳሴ አብዮቱ ጅማሬ ነው›› ሲሉ አወጉን፡፡ በማህበራዊ ሚዲያዎች፣ በጋዜጦችና መፅሄቶች ስናይ የነበረውን የውድድር ሳይሆን የመበላላት ፖለቲካ ‹‹የተቃውሞው ጎራ አባላትም ሆኑ የገዢው ፓርቲ ሰዎች በአንክሮ ሲከታተሉት የነበረ ዴሞክራሲያዊ ውድድር ነው›› ሲሉም ወጋቸውን ቀጠሉ፡፡ ‹‹ይህ እንቅስቃሴ አንድነትን ወደተሻለ ከፍታ የሚወስደው ከመሆኑም ባሻገር ልክ እንደ አረቡ አለም አብዮት ወደ ሁሉም የተቃውሞ ጎራ የሚዛመት አዲስ መንፈስ ነው፡፡" ሲለም የወጋቸውን ትንቢት አሳደጉ፡፡

መበላላቱን ሲያለሰልሱ ደግሞ ‹‹ምንም እንኳን በተወሰነ መልኩ በዴሞክራሲያዊ ውድድርና በውስጣዊ መከፋፈል መካል ያለውን ልዩነት በትክክል ያልገባቸው ወይም እንዲገባቸው ያልፈለጉ አንዳንድ ሰዎች የሚፈጥሩት ችግር የነበረ ቢሆንም አጠቃላይ እንቅስቃሴው ሲታይ ግን በኢትዮጵያ የፓርቲዎች ታሪክ ውስጥ በአዲስነቱ፣ በፈር ቀዳጅነቱና በአንፀባራቂነቱ የሚታወስ ነው›› ሲሉም ያልሆኑትን እና የማይችሉትን የመሆን የህልም ወጋቸውን አወጉ፡፡

ይህን የመበላላት እንቅስቃሴና ከላይ በተመለከተው አግባብ የምርጫ ቦርድ ላይ የተላከከውን ያልተፈጠሩበት የከሸፈ ፖለቲካ ‹‹ለሌሎችም አርአያ የሚሆን›› ነው ሲሉም

ተዘባበቱብን፡፡ ይህንና መሰል ይዘት ያላቸውን ወጎች ሲያወጉን የነበሩ በሁለቱም ፓርቲዎች ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ አመራሮች ያሉት ሁሉ እዳልሆነ ሲሆንና ጨዋታው ሲፈርስና ዳቦውም ሲቆረስ እንዳልታበዩ፣ እንዳልተዘባበቱ ሁሉ ከፓርቲያቸው ከማፈንገጥና በበቃኝ ከመውጣት ጀምሮ ‹‹የምርጫ ቦርድ ሴራና የገዢው ፓርቲ ደባ ነው›› ወደሚለው የማካኛ ወግ ተሸጋገሩ፡፡ ከፊሎቹ ደግሞ ያሉት ሁሉ ባይሆንና ባይሰምር ገዢው ፓርቲ ላይም ሆነ የምርጫ ቦርዱ ላይ ከማላከክ ባይቦዝኑም ትክክለኛውን የተበላሸና ያልተጠና የአሰላላፍ ወግም ለማመን በሚመስል ትንቅንቅ ውስጥ ሆነውም ስለነዚያ "ፈርቀዳጅ፣ አርአያ፣ አንፀባራቂና" ወዘተ ስላሏቸው ፓርቲዎች ማውጋታቸውን ግን አልዘነጉም፡፡

ፓርቲዎቹን በተመለከተ ጮቤ ረግጠው ሚስጥር የሌለውን፣ በህብረቃል በሰምና ወርቁ ያልተበጀውን ቅኔ ሲዘርፉልን ከነበሩት መካከል አንዱና ዋነኛው የአንድነቱ ከፍተኛ አመራር የሆኑት አስራት አብርሃም ናቸው፡፡ እነዚያ ያጀገናቸው ፓርቲዎች እንዲህ ምስቅልቅል ውስጥ መግባታቸው ደግሞ በመርህ ደረጃ ውህደቱ በከሸፈ ማግስት ቀደም ብለው ያመኻኙበትን ወግ የማይመጥን እና ከማመኸኛው የገዘፈ የፓርቲዎቹን ፀረዴሞክራሲያዊነት የተመለከተ ወግ ያወጉን ዘንድ ግድ አላቸው፡፡ ከወጎቻቸውም ከመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አኳያ ሁነኛ ማጠየቂያ የሆኑትን ወስደን በአዲስ መስመር መልሰን እናወጋ ዘንዳ ግድ ይለናል፡፡

የተቃውሞ ፖለቲካ የለውጥ እና የመነሳሳት መንፈስ አካባቢ መሆን ሲገባው በተለያዩ ጊዜያትና ሁኔታዎች የከሰሩና የከሸፉ ፖለቲከኞች መደበቂያ ዋሻ ብቻ እንዳልሆነ የሚጠቁመው በአቶ አስራት አብርሃም ብእር የተከተበልን የፓርቲዎቹ ወግ በእነዚህ ፓርቲዎች ውስጥ አባታዊነት፣ ቡድናዊነት እና ራዕይ አልባነት እንደሚስተዋልም ጥምር በመረጃ አስደግፎ ያወጋናል፡፡ በእነዚህ ፓርቲዎች ውስጥ በዴሞክራሲ መርሆ መሰረት የፓርቲ አባላት በፓርቲያቸው ያላቸው መብት እኩል መሆን ሲገባውና ከየትኛውም የፓርቲያቸው አባልና አመራር ጋር የሚኖራቸው ግንኙነትም በእኩልነትና በነፃነት መርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ሲገባው ፊውዳላዊ የሆነ የጌታና ሎሌ ግንኙነት መሆኑንም የፓርቲዎቹ ወግ ያስገነዝበናል፡፡

በዚህ ብቻ የማያበቃው የፓርቲዎቹ ፀረዴሞክራሲያዊነት ባህሪይ መገለጫ የአንድ ግለሰብ ወይም የተወሰነ ቡድን ምንዝር ሆኖ መኖርን በሚያስቡ አባላት የተሞሉ መሆናቸውን የሚጠቁመው ከራሳቸው ብእር የደረሰን ወግ ነው፡፡ በምርጫ ቦርዱና በገዢው ስርዓት ለይ

ሲያማኻኑ ከነበሩት ፓርቲዎች የአንድነት ከፍተኛ አመራር ‹‹በተቃውሞ ፖለቲካ ውስጥ ያለው ትልቁ ችግር የዴሞክራሲና የሊበራሊዝምን ባህል ጠንቅቆ ያለማወቅ፣ በአጠቃላይ የፖለቲካ እውቀት ማነስ ነው፡፡›› በማለት ከማመኻኛዎቹ በላይ የገዘፈውን እና የፖለቲካ ሀሁ የሆነውን ችግር ግና እንዳልተላቀቁ ያወጋናል፡፡

እነዚያ "ምህዳር ጠበበ፣ ተለጣፊ ፓርቲዎች አስቸገሩን፣ የስብሰባ አዳራሾች አጣን፣ ሰላማዊ ሠልፍ ተከለከልን" ወዘተ የሚሉት፣ የራሳቸውን ችግር ወደሌላ በማላከክ የ23 ዓመታት ወጎቻቸው የምናውቃቸውን ጉምቱ የተቃውሞው ጎራ አመራሮች በተመለከተም *የሁለቱ ፓርቲዎች ወግ* እውነታውን  እንዲህ ይተርክልናል፡፡ ‹‹ሲጀመር በየፓርቲዎቹ ያሉት መሪዎች ከፍተኛ የግል የሥልጣን ጥም ያለባቸውና በደመነፍስ ፖለቲካውን መምራት የሚፈልጉ፣ ራዕይ አልባ መሪዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም አሁን ልናካሂደው እያሰብነው ያለውን ፍፁም ሰላማዊ የሆነ፣ ዘመናዊ የለውጥና የህዳሴ እንቅስቃሴ ለመምራት አቅም አላቸው ተብሎ የሚተሰብ አይደለም፡፡ እኔ በበኩሌ በፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ በዶ/ር መራራ ጉዲ፣ በኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው እና በመሳሰሉት የስልሳው ትውልድ ቅሪቶች ትግሉ ተመርቶ ለውጥ ያመጣል ብዬ አላስብም፡"፡ የሚለውን እና ቃል በቃል የተመለከተውን የፓርቲዎቹ ወግ በፋክት ቁጥር 59 ነሀሴ 2006 መፅኄት ያሰፈሩልን የአንድነቱ አመራር፤ በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎቹን ‹‹እንኳንስ ኢትዮጵያን የምታህል የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች ሃገር እና 80 ሚሊዮን ህዝቦቿ ይቅርና እራሳችሁንም፣ በቅጡ መምራት የማትችሉ ናችሁ፡፡›› ሲል የነበረውን ‹‹ፌዝ›› ብለው ሲያጣጥሉ የነበሩ ፖለቲከኞች መሆናቸው የሁለቱን ፓርቲዎች ወግ ማጠየቂያችንን የትክክለኛነት ደረጃ ከፍ ያደርግልናል፡፡ የቅድመ ውህደቱን ሂደት ልክ አይደለም ሲሉ ያሂሱ ወገኖችን በካድሬነትና በተለጣፊነት ፈርጀው የእሬቱ ውድድሩን "ፈር ቀዳጅና አርአያነት ያለው" ሲሉ ያሞካሹት ሃይሎች ‹‹ራዕይ አልባ›› ባሏቸውና ‹‹በደመነፍስ ፖለቲካን ሊመሩ የሚሹ›› ባሏቸው ሃይሎች እንዲሁም በውስጥ በተነሳው የሥልጣን ሽኩቻ አንዳልነበርና እንዳልጠበቁቱ ሲፈራርስ ወጋቸውን እንዲህና ከላይ በተመለከተው አግባብ በካድሬነትና ተለጣፊነት ከፈረጇቸው ወገኖች ጋር አስማሙ፡፡

‹ከኛ ወዲያ ፖለቲካን ላሳር ከሚል የግል ስሜትና ፍላጎት ወጥተው እስኪ ደግሞ ከታች ያሉት አዳዲስ ትውልዶች ይምሩትና እንየው›› በሚል ወግም ጉዳዩን አፀደቁ፤ ይህንን ወግ የነገሩንና የወጉ ተጋሪዎች በተለያየ መንገድ እንደተረኩልን የውስጥ ለውጡን የሚሹት

በፖለቲካው ዘገምኝነት እጅግ ስለተሰላቹ የታቃውሚው ፖለቲካው በአዙሪት ሽንፈት ውስጥ ስለገባ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም አንጋፋ የሚሏቸው ፖለቲከኞች እንቅፋት ከመሆን ገለል እንዲሉ የሚጠይቀው የፓርቲው ወግ ብቃት የነበረው የቀደመው ትውልድ በልዩ ልዩ መንገድ እየተገለለና አሁን የቀሩቱ "አመድ" ብቻ እንደሆኑም ይገልፃል፡፡ እነዚህ አንጋፋ የተባሉትና አመድነታቸው የተነገረላቸው የተቃውሞ ፖለቲካ አመራች ኋላቀር ከሆነው የጠልፎ መጣል ሴራ እና የፍረጃ ፖለቲካ መውጣት እንዳለባቸው ተማፅኖ የሚያቀርቡ ፓርቲዎች ወግ ከሁሉ በላይ ለሃገርና ህዝብ ማሰብ ያለባቸው እንደሆነ በመግለፅ ለግል ጥቅም የመቆማቸውን ከፍ ያለ ደረጃ በአግቦ ሹክ ይለናል፡፡

ይህ እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ የእናቴ መቀነት ጠለፈኝን እና ከላይ የተመለከቱ ማመሃኛዎችን ለሚደረድሩ ሃይሎች በማጠየቂያነት የተመለከተ ጭላፊ የሴራ ፖለቲካ ወግ ነው፡፡ ይህ በመሆኑና ጉምቱዎቹ እንቅፋት መሆናቸውን ገልፀው ከአንድነቱ ቤት ከወጡቱ 5 አመራሮች ዛሬም ድረስ አንደኛው ገፍተውበት ክሽፈቱንም ሆነ መፈረካከሱን ኢህአዴግ ላይ መለጠፋቸውን ተያይዘውታል፡፡ ማመኻኛው ሳያንሳቸው ልጠፋቸውን ኢህአዴግን ከወታደራዊ ጁንታው ደርግ ጋር አነፃፅረውት መሆኑ ግን ግር ይላል፡፡ ግለሰቡ ደግሞ የአንድነቱ የድርጅቱ ጉዳይ ኃላፊ የሆኑት አቶ ዳንኤል ተፈራ ናቸው፡፡ የራሳቸው በጩኸትም ያልበረደ እሳት እንዲህ ከላይ ተመልክቶ ሳለ ‹‹የህወሃት /ኢህአዴግ የመጨረሻ ጩኸት›› ሲሉ የተሰላቸውን ወግ ይጠርቁልናል፡፡ ይህን የሁለት ፓርቲዎች ወግ ተቃውሞውን እና የገዢውን  ጩኸት አልባ ጩኸት የተመለከተ በክፍል ሁለቱ የፓርቲዎች ወግ ትርክታችን በሚገባ እናሂሰው ዘንዳ በቀጠሮ እንለያያለን፡፡